# ደም መገበርን ተለማመድነው

በሃገራችን ኢትዮጵያ ፍትህ ሰላም ኡልነት ብልጽግና እንዲሰፍን የሃገራችን ሏላዊነትና አንድነት እንዲጠበቅ በተደረገው ትግል ውስጥ ህይወታቸው ያለፈው ዜጎቻችን ቁጠር ምን ያህል ዪሆን? ዪህ እንጊዲህ እንደሃገርና ህዝብ ቆመን በፖለቲካ ሳቢያ ብቻ ያለፈውን ህይወት ማለቴ ነው።ከንጉሱ ጅምረን በደርግና በህዋያት ኢሃዴግን ዘመን የተሰዋው ህይወት ቁጥር ምንያህል ነው? መቶ ? አንድሽህ ? መቶ ሽህ ?ሚሊዮን ? ማን ያውቀዋል?

አዎ ፍትህ በሌለበት ነጻነት በሌለበት ፍትህንም ሆነ ነጻነትን ለመግኘት መስዋእትነትን መክፈል የህብረተሰብ ህልውናና እድገት ውስጥ የሚታይ ክስተት ነው። ዛሬ በሰለጠኑት ሃገሮች አንዲት ነፍስ ዋጋዋ እጅግ በጣም ቢዞ ነው። በአደጋና አልፎ አልፎ ከከፋት ከሚመነጭ የግለሰቦች ባህርይ የተነሳ ህይዎት ዪተፋል ያም ቢሆን የተፋው የእያንዳንዱ ሰው ህይወት ቀሪውን ሊያድን በሚችህል ህጋዊና ሙዋችንም ከንቱ የማያስቀር በሚሊዮኖች የሚቆተር ገንዘብ ፈሶበት ተገቢው ምርመራና የምርመራውም ውጠት ለህዝብ ዪታውቃል። የሃገርችህውን ጥቅም ለማስጠበቅ በጦርነት የወደቁ ከ 40 ና 50 አመት በሁዋላም ቢሆን አጽማቸውና ታሪካቸው በክበር እንዲያርፍ ዪደርጋል። በምንም መልኩ ቢሆን ሃገራችንን ለማነጻጸር ፈልጌ አይደለም።አባቶቻችን ከቅኝ ገዚዎችና ወራሪዎች ጋር ባደረጉት ተጋድሎና በኛ ዘመንም ሃገራችን አትቆረስም ብለው በኤርትራ በረሃና በትግራይ የረገፉት የኢትዮጵያ ሊጆች ከጭቆና ለመላቀቅ መገንተል ነጣነትን የሚያጎናጽፍ መስሎአቸው በኤርትራ ተራሮች የወደቁት ኤርትራውያን (ለእኔ ኢትዮጵያውያን)በትግራይ መጀመሪያ በትግራይ ነጻነት ስም በሁዋላም በእትዮጵያ የዲሞክራሲና የብሄረሰብ እኩልነት ስም የወደቁት የትግራይ የአፋር የሲዳማ የወላይታ የከምባታ በአጥቃላይም የደቡብ ልጆች በኡጋዴን በረሃ የወደቁት የኢትዮጵያውያን ሶማሌ ሊጆች የጋምቤላ የቤኒስሃንጉልና የህዝባቸው ቁጥር ትልቅነት ተሳትፎአችህውንም ሆነ መስዋእትነታቸውን የበለጠ እንዲያደርግ የመጣው ፖለቲካ ሁሉ ዋነኛ ሰለባ የሆኑት ዛሬም እየሆኑ ያሉት የኦሮሞና የአማራ ሊጆች በድምሩ በውብ ቁዋንቋና ባህል የተዋበችህው  የአንዲት ኢትዮጵያ ደም ክፋይ ልጆች በቅይሽብር በነጭ ሽብር በተገንጣይ በአስገንጣይ በስብረተኛነት በጎጠኝነት ፖለቲካ ያለቁት ምን ያህል ዪሆኑ?

ሁሉም በየጎራው የከፈሉትና የገበሩት ድም የተሻለ ሃገርና የተሻለ የህዝብ ህይወት ፈጥሩ?ወይስ ገና አሁንም የፈሰሰው ድም አልበቃምና ለሌላ ግብር እየተዘጋጀን ነው?እኮ ለምንድነው ያን ያህል ህይዎት የገበርነው? የህይዎት ግብሩ ለውጥ አላመጣም ማለት ግን አይደለም ። በርግጥ  ቀድሞም በየዋህነትም ዪሁን በአስተሳሰብ ዝቅተኝነት  ጥቂቶች የራሳቸው ያደርግዋት ሃገርና ህዝብ ዛሬ ሳይንሳዊ ትንተና በሚሰጣቸው የፖለቲካ መገለጫዎች አሽብርቀው የህብረተሰቡን ስጋውን ሳይሆን ነፍሱንም ጭምር እይተቆታተሩ ያሉበት ዘመን ላይ ደርሰናል።ጥቂቶች የእኛ የሚሉዋት ሃገር እየገነቡ ነው።ብዙሃኑ ግን ቢችህገርም በተስፋዋ የሚኖርባትን ሃገርም ባለቤትነቱን ተነጥቆ የበይ ተመልካጭች ሆኖአል። ታዲያይህ ሁሉ  ድም የፈሰሰለት ሃገር ህዝብ ለሱ የሞተለትንና የሚከፈልለትን ዋጋ ተገንዝቦአል?  ቢያንስ ለኔ ሲል ነው የሞተልኝ ዪላል ወይ? የሞቱለቱን ሊጆችሁን ፍሬ በልቶ ለማጣጣም እንጂ ፍሬውን ለመንከባከብ የማይችህል  ከሆነና ነጻነቱን የሚለካው በየቀኑ ሰልፍ እየወታ  ዛሬ ዪህን ያህል ሞተ ብሎ የሚያርፍ ከሆነና ፖለቲከኖቻችሃችንም ለውጥትንና መስዋእትነትን   ዪህን ያህል ሰው ሞተ እያልን አስከሬን በመቁተር  ፊስ ቡክ በማድመቅ ዝናችንን ከመገንባት ያለፈ ለውጥ የማናመጣ ከሆነ ህጻናቱ ለምን

ዬሙቱ ?  ገዳዮች በደም መፍሰስ  በመግደል በማሰር በማሰቃየት ሃገርን ከጥፋት ለማዳን ነው የሚል አንዱን እየገደልክ ሌላውን የማዳን የድንቁርናና የእብሪት ፖለቲካ ሲጨፍሩ እያየን ወደፊት ስንት ደም እንዲፈስ እያዘጋጀን ነው? ኧምሮአችን በማስወገድ በመግደል በማጥፋት በመደምሰስ ቃላቶች ተገንብቶ መወያየት መነጋገር መቻቻል መተራረም መወቃቀስ ልህዝብ ጥቅም ሲባል ስጥቶ መቀበል የሚሉት በጎ መንፈሶች የሚያርፉብን መቼ ነው?

በፖለቲካ ሳቢያ መገዳደል ምንጩ ሁዋላ ቀርነትና ከፍተኛ ተጠቃሚነት ፍላጎት ነው። ዛሬም ንጥሱሃን ህጻናት ሰለባ እየሆኑ ያሉት ለዚሁ ነው። ገዳዮችም አስገዳዮችም በህዝብ ስም የምነነግድ ችግራችንን በአንድ አላም አብረን ከተሰለፍነው ጋር እንኳን ቁጭ ብለን የመነጋገር ድፍረቱ የሌለን የራሳችንን ተክለሰውነት እንጂ የእያንዳንዱ ሰው ህይውት ግድ የማይለን ፖለቲከኖች ነን ። ህብረተሰባችንም ብፖለቲካ ሳቢያ ሞትን አለማምደነዋል። ያማ ባዩሆን እንኳን መቶ ሰው በግፍ ተገድሎ አንድም ሂይዎት ቢሆን ህዝባው ማእበልን ያመጣል። ዛሬም በየፌስቡኩ ፊታችን የሚያበራውን ፎተግራፍ እየለጠፍን ሚስኪን ደሃውን አቅጣጫውን በማያውቀው ፖለቲካ ውስጥ ድሙን ለሰይጣኖች  እንዲገብር ከማድረግ ይልቅ  የጎደለንና ትግሉ የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል እንዲሆን በማድረግ የማንኛውም እትዮጵያዊ ደም ዋጋ ያለው መሆኑን የተገነዘበ የተደራጀ ህዝባዊ መሰረት ያለው የፖለቲካ ስብስብና ራእይ ሊቀድም ዬገባል። ለጥቂት የህዋሃት የኦፒዶ የብ አዴን የደቡብ ቅምጥሎች ወይም ተቃዋሚ ነን ብለው በንዲህ አይነቱ ሃገራዊ አደጋ ጊዜ እንኳን ሊዩነታችህውን በማቻቻል ሃገራዊ አጀንዳ መቅረጽ ላልቻሉ የስልጣን ጥመኞች አንዲት ህይዎት መገበር የለበትም ። በተጨመላለቀ የፖለቲካ አስተሳሰብ የሚገበር ህይዎት ከንቱ ሆኖ እንዳይቀርና ዉቲታማ እንዲሆን የጎደለንን የመሪ ፖለትካ ድርጂት በምንም መልኩ ማምጣት አጣዳፊ ተግባር ሊሆን ዬገባል።

Gishag70@yahoo.com